# ፪ሚሌኒየም!

ብናኝ ሴኮንዷ ታምቃ
ደቃቃ ደቂቃ ተጣብቃ
ሠዓት ሆና ሣታበቃ
ቀን ቆጠርን በፈረቃ::

ቀናትም ሳምንት አስከትሎ
ሳምንታት ወራት ላይ በቅሎ፣
ወራት ዓመት ወለደ
ከእድሜ አንድ ነጎደ::

ዓመት ከዘመን ተሰፍሮ
ከ«አማአት» ተቆጥሮ፣
ዓለም- ዓለም እንደሆነ
ሁለት ሚሊየን ደፈነ::

ከጌታ ልደት በኋላ
ሁለት ሺህ ብትሞላ፣
በዚህ ሁሉ ዓመታት
ሠማይ ምሰሶ የላት፣
በዚህ ሁሉ ዘመናት
ምድር በዛቢያዋ ናት::

ሳይከብድ ሠማይ - ለምድር
አብረው ከርሞል በፍቅር::

ዘመነኛው እያለፈ
ትውልድ እየጎረፈ፣
የተረገዘ ተወልዶ
ያደገ ወልዶ - ከብዶ
ሁሉም የራሱን ፈረቃ
ተንፍሶ እያበቃ
ሞቶ አየተቀበረ
ሁለት ሚልዮን ቆጠረ::

ሠው በምድርና በሠማይ
በለሥልጣን ሆኖ የበላይ፣
የራሱን ህግ ፈጥሮ
እንደየ ወጉ ተዳድሮ
ተጣብቶና - ተፋቅሮ
ኖረ የራሱን ኑሮ::

አምላክ የፍጡራን ፈጣሪ
የምድር የሰማያት ሠሪ፣
ዓለም በጎደላት ቦታ
ልግስናውን አልገታ::

ለእኛ ግን ለአፍሪቃ
ሰጦታው ሣትሆን ቀኑ ርቃ፣
ከኑሯችን ስቃይ ፈልቆ
ሕይወታችንን ቁልቁል ደፍቆ፣
መከራን ተጎንጭተን
ኖረን ሞትን ሳይመችን::

ግን ጥንድ አማአት የኖረባት
ሥቃይ - መከራ ቆጥሮባት፣
ጨፈረ ደሰተኛ መስሎ
ውስጡ በቁጭት ከስሎ::
ያሐገር ያለህ እያለ
አምሽቶ አብሮ ዋለ!
በወላጆቼ እጅ አድጌ
በትምህርት ተመንድጌ
ሃብት ቢጤም አብጅቼ
የምወዳትን አግብቼ
ባልኖርም ያው አርጅቼ
ሰባ ችቦ አብርቼ፣
ልጅ ወልጄ ብድርም
የረባ ለውጥ አላየሁም::
በቁም የሉ ወገኖቼ
የእድሜ እኩያ አቻዎቼ::
በእውነት! ስለእውነት ይመስክሩ
እንዴት እንደከረምን እንደምን እንደኖሩ::
ወደኃላ እየዞርኩ
ወደፊትም እያለምኩ
አዘንኩ!
አፈርኩ!
በአይኔ እያየሁ የሚያሳፍር
እንዴት ጮቤ ልጨፍር?
ዝም አልኩኝ በትዝብታ
ለእንቀጣጠሸ እለት ማታ::
የህዝቡና ውክሉ- መንግስቱ
ተለያይቶብኝ ስሜቱ፣
ማምሸት ቢያቅታቸው ተቻችሎ
ማንነታቸውን ያህል አህሎ፣
ተገረመብኝ ውስጤ
ባጣ ጊዜ የኔ ቢጤ::
እናም ሰለሞን እንዳለው ድሮ
የእውን ቃሉ ውስጤን ጭሮ ፣
«ሴኮንዶች ... ከንቱ
ደቂቃዎች ... ከንቱ
ሰኣቱና - ሣምንቱ
ወራትና - ዓመቱ
ዘመናት - አማአቱ
ሁሉ የከንቱ ከንቱ::»
ብቻ የመኖር ያህል ተንፍሰን
ሁለት ሚሊዎን ጨረስን::
ዝም አልኩ እንጂ በእርጋታ
እንዴት ልጨፍር ያንን ለታ?
በእርግጥ መልካም ተመኝሁላት
ሥቃይ - መከራ ቢያበቃላት::

ድፍን ምዓተ- ዓመት በጦር ለከረመ
ድፍን ምዓተ- ዓመት በረሐብ ለደከመ፣
ድፍን ምዓተ- ዓመት በሽታ ለጋጠው
ድፍን ምዓተ- ዓመት እጦት ላናወጠው
ይህ ሚሊንየም ምንድነው ያመጣው?
ድፍን ምዓተ- ዓመት ቀለም ላልቆጠረ
መልካም አስተዳደር ይመኝ ለነበረ
ይህ ሚሊንየም ምን በእጁ አኖረ?
እኔ ጠይቃለሁ ራሴን ደጋግሜ
እስቲ ምኑ ጋ ነው?.... ጥቅምሽ!
ጥቅምህ! ጥቅሜ
ይህን ሁሉ ዞረን ርቀን ካስተዋልነው
የሚሊንየሙ ችሮት አንድና አንድ ነው።
መልካም አስተዳደር
በጋራ ለማደር።
መልካም አስተዳደር
ሠላምን ለመፍጠር።
መልካም አስተዳደር
በፍቅር ለመኖር።
መልካም አስተዳደር
በሽታን ለመቅበር።
መልካም አስተዳደር
ለድንቁርና ጠር።
መጪውን ሚሊንየም በደስታ ለማክበር
ይህ ትውልድ ድርሽ አለው እውነት ለመናገር።
አደራ ካለብን በሉ እንነጋገር
መጣባቱ ይብቃ እስቲ እንፈቃቀር።
በፈጠራችሁ!!!!! እንባባል ይቅር
በዚህ ከተስማማን ሕዝብ ሁሉ ይጨፍር።

*መስከረም አንድ ማታ 2000*
ምስጋናው ከበደ ጨኮ